# <u>የሙስሊም ጎረቤታችንን እንዴት እንውደድ?</u>

መልካም ለማድረግ እና ለመሳሳት ብዙ እድሎች እንዳሉ ሁሉ÷ ለዚህ ጥያቄም አያሌ መልሶች አሉ። “ፍቅር ባልንጀራው ላይ ክፉ አያደርግም” (ሮሜ 13፡10)

“ፍቅር ሁልጊዜ ይታገሳል፤ ሁልጊዜ ያምናል፤ ሁልጊዜ ተስፋ ያደርጋል፤ ሁልጊዜ ጸንቶ ይቆማል።” (1 ቆሮንቶስ 13፡7)። እንደሚመስለኝ በእኛ ዘመን ትኩረት ሊሰጣቸው ሚገቡ ነገሮች እዚህ ላይ አሉ።

የሚጠሉንን ስለመውደድ በመጠቀሱ ሁሉም ሙስሊሞች ለክርስቶያኖች ጠላትነት ያሳያሉ ማለት አይደለም። በፍጹም። በተቃራኒው÷ አብዛኛውን ጊዜ እንግዳ ተቀባይ፣ ደግ እና ሩህሩህዎች ናቸው። ማንኛውም ሰው (ከየትኛውም ሀይማኖት ወይም ሀይማኖት የለሽ ሊሆን ይችላል) ቢጠላን፣ ቢጎዳን ዋናው ቁምነገሩ እኛ መውደዳችንን መቀጠል እንዳለብን ማወቁ ላይ ነው።

በዚህ በእኛ ዘመን ተጨማሪ ማብራርያ ያስፈልገናል። ፍቅር አካላዊ ፍላጎቶችን ለማሟላት÷ መልካምነትን ተግባራዊ በሆኑ መንገዶች እንድናደርግ ይጣራል ብዬ ስናገር÷ ሰዎች ከእስልምና ወደ ክርስትና በመምጣታቸው ላይ የተደገፈ እርዳታ መሆን አለበት ማለቴ አይደለም። ይልቁንም ተግባራዊ ፍቅር÷ ለክርስቶስ ፍቅር አይነተኛ ምስክር ነው። ምስክርነት ደግሞ ይበልጡን በሚፈለግበት ስፍራ መነፈግ የለበትም።

ሰዎችን በኃይል ወይም ደግሞ በገንዘብ እንዲለወጡ ማድረግ ከእምነት የማዳን ባህርይ ጋር የሚፃረር ነው። አዳኙ እምነት÷ ኢየሱስን እንደ አዳኝ፣ ጌታ እና ታላቅ ሀብት በማመን እና በመቀበል የሚገኝ ነፃ ስጦታ ነው። እርሱ ወደ ሀብት የሚወስድ መንገድ ሳይሆን ራሱ ሀብት ነው።

1. ቢወዷችሁም÷ ቢጠሏችሁም÷ የክርስቶስ በረከት በሙላት በእነርሱ ላይ እንዲሆን ጸልዩ።
    - **ሉቃስ** 6፡28-የሚረግሟችሁን መርቁ፤ ለሚበድሏችሁም ጸልዩ።
    - **ሮሜ** 12፡14-የሚያሳድዷችሁን መርቁ፤ መርቁ እንጂ አትርገሙ።
    - **1ቆሮንቶስ** 4፡12- ሲረግሙን እንመርቃለን።
2. አካላዊ ፍላጎቶቻቸውን ተግባራዊ በሆነ መልኩ በማሟላት መልካምን አድርጉላቸው።
    - **ሉቃስ** 6፡27-ጠላቶቻችሁን ውደዱ፤ ለሚጠሏችሁም መልካም አድርጉ።
    - **ሉቃስ** 6፡31-ሰዎች እንዲያደርጉላችሁ የምትፈልጉትን እናንተም አድርጉላቸው።
    - **1ተሰሎንቄ** 5፡15-ማንም በክፉ ፋንታ ክፉ እንዳይመልስ ተጠንቀቁ፣ነገር ግን እርስ በእርሳችሁም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ሁል ጊዜ መልካም የሆነውን ነገር ለማድረግ ተጣጣሩ።
    - **ሮሜ** 12፡20-ጠላትህ ቢራብ አብላው፤ ቢጠማም አጠጣው። ይህንን በማድረግህም የእሳት ፍም በእራሱ ላይ ትከምራለህ።

3. ሲበድሏችሁ አጸፋ አትመልሱ።

- **1 ጴጥሮስ 3፡9-** ክፉን በክፉ ወይም ስድብን በስድብ ፋንታ አትመልሱ፣ በዚህ ፋንታ ባርኩ፤ ምክንያቱም እናንተ የተጠራችሁት እንደዚህ ያሉትን ነገሮች እያደረጋችሁ በረከትን ለመውረስ ነው።

- **ሮሜ 12፡17፣19-** ለማንም ክፉን በክፉ አትመልሱ፤ በሰው ሁሉ ፊት በጎ የሆነውን ነገር ለማድረግ ትጉ። ወዳጆቼ ሆይ፤ ለእግዚአብሔር ቁጣ ፈንታ ስጡ እንጂ አትበቀሉ፤ "በቀል የእኔ ነው፣ እኔ ብድራትን እመልሳለሁ" ይላል ጌታ ተብሎ ተጽፏልና።

4. በእናንተ በኩል በተቻላቸው አቅም በሰላም አብራችሁ ኑሩ።

- **ሮሜ 12፡18-** ቢቻላችሁስ ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ።

5. የክርስቶስን እውነት በመንገር ከሐጢያትና ከፍርድ በደስታ ነጻ እንዲወጡ በጽኑ ፈልጉ።

- **ዮሐንስ 8፡31-32-**ኢየሱስም በእርሱ ያመኑትን አይሁድ እንዲህ አላቸው፡ "በትምህርቴ ብትጸኑ እናንተ በእውነት ደቀመዛሙርቴ ናችሁ፤ እውነትንም ታውቃላችሁ፤ እውነትም ነጻ ያወጣችኋል።"

6. መንገድ የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን እያሳያችኋቸው÷ በመንግስተ-ሰማይ እንዲቀላቀሏችሁና ከአብ ጋር እንዲሆኑ አጥብቃችሁ እሹ።

- **ሮሜ10፡1-** ወንድሞች ሆይ… የልቤ ምኞት፣ እግዚአብሔርንም የምለምነው እንዲድኑ ነው።

- **ዮሐንስ 14፡16-** ኢየሱስም እንዲህ አለው፤ "መንገዱ እኔ ነኝ፤ እውነትና ሕይወትም እኔው ነኝ፤ በእኔ በኩል ካልሆነ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።"

7. ሒሶቻችሁና ድጋፎቻችሁ በተዛቡና በተሳሳቱ አመለካከቶች ላይ ሳይሆን÷ እውነተኛ በሆነ መረዳት ላይ ይመሰረት ዘንድ የሚሉትን ለመረዳት ፈልጉ።

- **1 ቆሮንቶስ 13፡6-** ፍቅር ከእውነት ጋር እንጂ በአመጽ ደስ አይሰኝም።

8. የአለምን ኃጢያት በሞቱና በትንሳኤው ያስወገደውን ኢየሱስ ክርስቶስን ያልተቀበሉ ሁሉ በእግዚአብሔር ቁጣ እንደሚጠፉ በእንባ አስጠንቅቋቸው።

- **ዮሐንስ 1፡12-** ለተቀበሉትና በስሙ ላመኑት ሁሉ ግን የእግዚአብሔር ልጆች የመሆን መብት ሰጣቸው።

- **ሮሜ 10፡9-** "ኢየሱስ ጌታ ነው" ብለህ በአፍህ ብትመሰክር፣ እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሳው ብታምን፣ ትድናለህ።

- **ፊልጵስዮስ 3፡18-** ከዚህም በፊት ደጋግሜ እንደነገርኋችሁ፣ አሁንም እንደገና ያውም በእንባ እነግራችኋለሁ፤ ብዙዎች የክርስቶስ መስቀል ጠላቶች ሆነው ይመላለሳሉ፡፡

9. "ሙስሊሞች እውነተኛውን አምላክ ያመልካሉ" በማለት ወደተሳሳተ አቅጣጫ አትምሯቸው፤ የሐሰትንም ተስፋ አትስጧቸው፡፡

ይህ ዐረፍተ ነገር÷ ለሁሉም ሠው÷ እውነተኛነታቸውን እግዚአብሔርን ለማወቅ፣ ለመውደድና ለማክበር ሙስሊሞች ስላላቸው ልብ አዎንታዊ ምስልን ያስተላልፋል፡፡

ነገር ግን ኢየሱስ÷ ሰዎች ለእርሱ በሚሰጡት ምላሽ ለእግዚአብሔር ያላቸውን ስፍራ የሚያሳይ እውነተኛ መለኪያ አድርጎ ይቆጥረዋል፡፡ እናም ሠው የእርሱን መለኮትነት እና ስለ ሰው ልጆች ኃጢአት ሞቶ መነሳቱን ካልተቀበለ፣ እውነተኛውን እግዚአብሔር እንደማያውቅ፣ እንደማይወድ እንዲሁም እንደማያከብር ግልፅ አድርጎ አስቀምጦታል፡፡

- **ዮሐንስ 8፡19-** ከዚያም፣ "አባትህ የት ነው?" አሉት፡፡ ኢየሱስም፣ "አባቴንም እኔንም አያውቁም፤ እኔን ብታውቁኝ ኖሮ አባቴንም ባወቃችሁ ነበር" ሲል መለሰላቸው፡፡
- **ዮሐንስ 5፡23-** ወልድን የማያከብር፣የላከውን አብንም አያከብርም፡፡
- **ዮሐንስ 5፡ 42-43** -(ኢየሱስም አለ) የእግዚአብሔርም ፍቅር በልባችሁ እንደሌለ አውቃለሁ፡፡ እኔ በአባቴ ስም መጥቼ አልተቀበላችሁኝም፡፡

ፍቅር፣ ሙስሊሞችን አሊያም ስለ ሙስሊሞች ግድ የሚላቸውን፣ ኢየሱስን በማንነቱ ሳይቀበሉ÷ እውነተኛውን አምላክ "ያውቃሉ" ወይም "ያከብራሉ" እና "ይወዳሉ" በማለት ወደ ስህተት አይመራም፡፡ እኛ የሰዎችን ልብ ማየት አንችልም፡፡ እውነተኛውን አምላክ እግዚአብሔርን ማወቃቸውን፣ማክበራቸውንና መውደዳቸውን እንዴት እናውቃለን? ኢየሱስን ለእነርሱ ለመስጠት ህይወታችንን እንሰጣለን፡፡ እርሱን ቢቀበሉት÷ እግዚአብሔርን ያውቁታል፣ ያከብሩታል እንዲሁም ይወዱታል፡፡ ካልተቀበሉት ግን አያደርጉትም፡፡ ለእግዚአብሔር የሚሰጡት ዋጋ መለኪያ÷ ለኢየሱስ የሚሰጡት ዋጋ ነው፡፡

በሉቃስ 10፡16 ላይ ይህ የኢየሱስ ሐሳብ ነው፡፡ "እናንተን የሚሰማ እኔን ይሰማል፤ እናንተን የማይቀበል እኔን አይቀበልም፤ እኔንም የማይቀበል የላከኝን አይቀበልም፡፡" እንዲሁም በዮሐንስ 5፡46 "ሙሴን ብታምኑ ኖሮ፣ እኔን ባመናችሁ ነበር፡፡"

ለሙስሊሞችም ሆነ ለሌላ ማንም ሰው ልናደርገው የምንችላው አንድ ታላቅ ነገር ቢኖር፣ መስዋዕትነት የተሞላ እንክብካቤን በማድረግ እና ስለ እነርሱ መከራን ለመቀበል በመፍቀድ÷ ከከንቱ አምልኮ (ማርቆስ 7፡7) ዘወር እንዲሉ በመማጸን÷ ስለ ኃጢአት ስለ ኃጢአት ይቅርታ እና ስለ ዘላለማዊ ህይወት ተስፋ ተሰቅሎ፣ ከሞት የተነሳውን ክርስቶስን እንደ አዳኛቸው ይቀበሉት ዘንድ ስለ ክርስቶስ ኢየሱስ ሙሉውን እውነት መናገር ነው፡፡

በዓለም ካሉ የሙስሊም ህዝቦች÷ ወንድሞችን እና እህቶችን ማፍራት ታላቅ ደስታችን ነው፡፡

**በመጋቢ ጆን ፓይፐር!**